


# ምን ዓይነት የሽግግር ሒደት?

# ለምን እና እንዴት?

**ለውይይት የቀረበ መነሻ ሐሳብ**


**ልደቱ አያሌው**


ሚያዝያ 30 ቀን፣ 2016 ዓ.ም

# የሽግግሩ ሰንጠረዥ ማብራሪያ

1 እነዚህ ሦስት አካላት አገሪቱን ወደ አዲስ የሽግግር ሒደት የማስገባት ዕድል ያላቸው ኃይሎች ናቸው። በመቶኛ የተገለፁት ቁጥሮች ደግሞ ሦስቱ ኃይሎች አገሪቱን ወደ ሽግግር ለመውሰድ ያላቸውን የዕድል መጠን ግምቶች የሚያሳዩ ናቸው። ቀሪው 70 በመቶ ለሽግግር ያለመብቃት እና ከህልውና ጥፋት መትረፍ ያለመቻል ዕድላችን ግምት ነው።

2 አገራዊ የሽግግር ሒደት ለረጅም ጊዜ የሚካሔድና አገሪቱን ከምትገኝበት የፖለቲካ ቀውስ አውጥቶ ወደ መረጋጋት ለማስገባት በፖለቲካ ኃይሎች፣ በልዩ ልዩ ተቋማትና ኮሚሽኖች፣ በሽግግር መንግሥት፣ በሕዝብ እና ሕዝቡን በየደረጃው በሚወክሉ አካላትና በመደበኛ መንግሥት ተሳትፎ ጭምር የሚካሄዱትን አጠቃላይ ተግባራት አካቶ የሚገልፅ ሰፊ ሒደት ነው።

3 አገር-አቀፍ የተኩስ ማቆም ስምምነት መንግሥት እና በአገሪቱ ያሉ ሁሉም ታጣቂ የፖለቲካ ኃይሎች የሚያደርጉትን ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት የሚመለከት ነው። ስምምነቱ በዘላቂነት ተኩስ ማቆምን፣ የፖለቲካ እስረኞችን መፍታትና ምርኮኞችን መቀያየርን፣ የአውድሂ አስፈፃሚ ኮሚሽንን ማቋቋምንና ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም መስማማትን የሚያካትት ይሆናል።

4 ቅድመ-ሽግግር አውድሂ በታጠቁና ባልታጠቁ በሁሉም የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች የሚካሔድ ሒደት ነው። ሒደቱ በዋናነት ምን ዓይነት የሽግግር መንግሥት ሊቋቋም ይገባል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የሽግግር ጊዜ ቃል-ኪዳን (ቻርተር) ለማርቀቅ እና ለማፅደቅ የሚካሔድ አገራዊ የውይይት እና የድርድር ሒደት ይሆናል።

5 የሽግግር መንግሥቱ አሁን በሥልጣን ላይ የሚገኘውን መንግሥት የሚተካ በአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎችና ሕዝቡን በየደረጃው በሚዎክሉ ሲቪክ ማሕበራት እና ግለሰቦች ተዋፅኦ የሚቋቋም ጊዜያዊ መንግሥት ይሆናል። ኃላፊነቱም- አገሪቱን አሁን ላይ ከገባችበት የህልውና አደጋ አውጥቶ ሰላምና የሕግ የበላይነት ወደ ሰፈነበት የተረጋጋ ሁኔታ ማሸጋገር ነው።

6 በ ሕዝብ የተመረጠ መደበኛ መንግሥት የሽግግር መንግሥቱ የሥራ ዘመን ሲጠናቀቅ በነፃና ፍትሀዊ ምርጫ የሚቋቋም ይሆናል። ሆኖም የሽግግሩን ሒደት የበለጠ ለማፅናት እንዲቻል በዚህ የመደበኛ መንግሥት የመጀመሪያ አንድ ወይም ሁለት ዓመት ጭምር የድህረ-ሽግግር አውድሂ በቀጣይነት ይኖራል።

# ምን ዓይነት የሽግግር ሒደት?

# ለምን እና እንዴት?

## ለውይይት የቀረበ መነሻ ሐሳብ

### *መግቢያ*

*ከስድስት ዓመታት በፊት ተጀመረ የተባለው "የለውጥ ሒደት" እንዳይመለስ ሆኖ ከሽፏል። "የለውጥ አመራር ነኝ!" በማለት ወደ ሥልጣን የመጣው የጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ አገዛዝ አገራችንን ወደ በጐ አቅጣጫ የማሸጋገር ዕውቀት እና ልምድ ብቻ ሳይሆን ቅንነት እና ፍላጎትም እንደሌለው ላለፉት ስድስት ዓመታት በተግባር ታይቷል።*

*የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አገዛዝ ከሕዝብ እና ከአገር ደህንነት በላይ የራሱን የሥልጣን የበላይነት በማስቀደሙ ምክንያት አገራችንን ከቀን ወደ ቀን ወደ ባሰ አዘቅት ውስጥ እያስገባት መሆኑ በገሃድ እየታየ ነው። በዚህ አገዛዝ ዘመን በእርስ-በርስ ጦርነት ከአንድ ሚሊየን በላይ የሚገመቱ ዜጐቻችን ሞተዋል፣ በዜጐች ላይ የሚፈፀመው ጭካኔ የተሞላበት ሁለንተናዊ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ከፍተኛ እና የማያቋርጥ ከመሆኑ የተነሳ ለዜና ዘጋቢዎችም አታካች ሆኗል፤ ከዐራት ሚሊየን በላይ የሆኑ ዜጐቻችን ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው ተሰደዋል፤ ከሀያ አምስት ሚሊየን በላይ የሆኑ ወገኖቻችን ለከፍተኛ ርሀብና እርዛት ተጋልጠዋል፣ ከተሜው በታሪክ ታይቶ በማያውቅ መጠን የከፍተኛ የኑሮ ውድነት ተጠቂ ሆኗል። ወደፊት ስለምንሆነው ስናስብም ሶማሊያን፣ ሩዋንዳን፣ ሶሪያን፣ የመንን፣ ወይም ሊቢያን "ልንሆን እንችላለን" ብለን መተንበይ ትርጉም አልባ የሆነበት ጊዜና ሁኔታ ላይ ደርሰናል። ምክንያቱም ባ'ለፉት ሦስት ዓመታት ብቻ በእነዚህ ሁሉ አገራት ከደረሰው በላይ የሕዝብ እልቂት እና ስደት ስለደረሰብን ስለ 'ነገ'አችን ማነፃፀሪያም አጥተናል።*

***በአጠቃላይ፡ አገዛዙ ሰላምና የሕግ የበላይነት ማስፈን ተስኖት አገራችን በመደበኛ ስርዓት ሳይሆን ቋሚ በሚባል ደረጃ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና በወታደራዊ ኮማንድ ፖስት የምትገዛበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህም ሁሉ ሆኖ አገራችን ከገባችበት ሁለንተናዊ ቀውስ መውጣት ተስኗት በአገዛዙ እጅ ላይ እየፈረሰች ትገኛለች።***

*ከዚህ በኋላ አገራችን ከፊቷ አፍጥጦ እየመጣ ካለው እየተጨራረሱ የመበታተን አደጋ መዳን የምትችለው በወቅቱ አገዛዝ እየተመራች በመቀጠል ወይም ሌላ ዙር የይስሙላ ምርጫ በማካሄድ አይደለም። አገራችን በአሁኑ ወቅት የምትገኘው ህልውናዋን በማጣት ጠርዝ ላይ ስለሆነና የገጠማት አደጋም በሥልጣን ላይ ባለው*

አገዛዝ የመቀልበስ ዕድል ስለሌለው ዘላቂ መፍትሄ ሊገኝ የሚችለው ሁሉን-አቀፍ በሆነ አዲስ የሽግግር ሒደት ብቻ ነው።

‘አዲስ የሽግግር ሒደት ይጀመር’ ሲባል የሒደቱ ዋና ተግባር የሚሆነው ሁሉን-አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ነው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ደግሞ እንዲህ በቀላሉ እውን ሊሆን የሚችል ተግባር ስላልሆነ “እንዴት ይቻላል?” የሚል መሠረታዊ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀሬ ነው። የሽግግር መንግሥት ማቋቋም በእርግጥም ቀላል ሥራ አይደለም። በተለይም ፅንፈኝነትና ብሔርተኛነት ገዥ አስተሳሰብ በሆኑበት በአገራችን ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ፣ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም እጅግ ፈታኝ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ምክንያቱም የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ከአንድ አገር መንግሥታዊ ሥርዓት ከፍተኛ ውድቀት በኋላ ሌላ አማራጭ በማጣት ብቻ የሚታሰብ የመጨረሻ አስቸጋሪ መፍትሄ ነው።

ቀደም ባሉት ዓመታት እኔም ሆንኩ አባል የነበርኩበት ፓርቲ ኢዴፓ፣ ‘የአገራችንን የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት ከሽግግር መንግሥት በታች የሆነ ሌላ አማራጭ አለ’ ብለን ባመንበት ወቅት በግልጽ የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ተቃዋሚ የሆነ አቋም ስናራምድ ቆይተናል። ነገር ግን ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.ም ሆነ የወቅቱ የጠ/ሚ ዐቢይ አገዛዝ በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ያቀረብናቸውን የመፍትሄ ሐሳቦች ሊቀበሏቸው ባለመቻላቸው የሀገራችን የፖለቲካ ችግር የበለጠ ውስብስብና እጅግ አደገኛ ወደ ሆነ ደረጃ ተሸጋግሯል።

የወቅቱ አገዛዝ የሕዝቡን የለውጥ ጥያቄ ወደ ዘላቂ ስኬት የመቀየር ዐቅምም ሆነ ፍላጎት እንደሌለው በበቂ መጠን ከአረጋገጥንበት ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ኢ.ዴ.ፓ፣ ኢ.ሀ.ን እና ሕብር-ኢትዮጵያ ፓርቲ “ከእንግዲህ የወቅቱ የሀገራችን ችግር ሁሉን-አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግሥት ከማቋቋም ባነሰ ሌላ አማራጭ ሊፈታ አይችልም!” የሚል አቋም ላይ ደርሰናል። ከዐራት ዓመታት በፊት ያነሳነውን የሽግግር ጥያቄ ቀደም ሲል የሚቃዎሙት ኃይሎች ብዙ የነበሩ ቢሆኑም አሁን ላይ ግን የአብዛኛዎቹ የፖለቲካ ኃይሎች ድጋፍ ያለው አጀንዳ ሆኗል። ነገር ግን በ2012 ዓ.ም የሽግግር መንግሥት መቋቋም አስፈላጊነትን በተመለከተ ተዘጋጅቶ የቀረበው የመነሻ ሰነድ ከተፃፈ ዐራት ዓመት ስላለፈው፣ በእነዚህ ዓመታት ውስጥም በአገራችን በርካታ አሉታዊ ክስተቶችና የፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ ለውጦች ስለመጡ ሰነዱን ከአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ እንደገናና እንደ አዲስ ሰርቶ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኗል።

በማንኛውም አካል የሚቀርብ ማንኛውም አይነት የመፍትሄ ሐሳብ ምንጊዜም ለውይይትና ለድርድር ክፍት መሆን እንዳለበት ቢታመንም፣ ከዚህ በኋላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም አንድ አማራጭ ሳይሆን የግድ ልንተገብረው የሚገባ የመጨረሻና ብቸኛ አማራጫ ሆኗል። አንድ አገርና ሕዝብ ከዚህ በታች በሆኑ ሌሎች አማራጮች ወይም በመደበኛ መንግሥት ችግሩን መፍታት ካልቻለ ወደዚህ ዓይነቱ ከባድ አማራጭ ለመግባትና ይህንን ከባድ ኃላፊነት ለመጋፈጥ ይገደዳል። ማንም አገር የተሻለ አማራጭ አጥቶና ከዐቅም በላይ በሆኑ ሁኔታዎች ተገዶ እንጂ እንዲሁ በቀላሉ የሽግግር መንግሥት ወደ ማቋቋም አማራጭ ሊገባ አይችልም። እኛም ወደን ሳይሆን በገጠመን አስገዳጅ ሁኔታ ይህንን ከባድ አማራጭ ለመቀበል እንገደዳለን። ምክንያቱም የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ቅሪት-አካል የሆነው የብልፅግና አገዛዝ ‘የቱንም ያህል በጥልቅ

እታደሳለሁ’ ብሎ ቢምልና ቢገዝት፣ የቱንም ያህል አደረጃጀቱንና መሪዎቹን ቢቀያይር መቼም ጊዜ ቢሆን መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ድርጅት አለመሆኑን ከበቂ በላይ በሆነ እና ፈጽሞ በማያከራክር መጠን ደግሞ ደጋግሞ በተግባር አረጋግጦልናል።

በአንድ የሽግግር ሒደት የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ከባድ ተግባር ቢሆንም ከሌሎች ተመሳሳይ ችግር ከገጠማቸው አገራትም ሆነ ካለፉት የሀገራችን የሽግግር ወቅቶች ጋር ሲገናዘብ ግን **በአሁኑ ወቅት በአገራችን የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችል የተሻለ አንፃራዊ ሁኔታ በሚከተሉት ሦስት ምክንያቶች አለ** ማለት ይቻላል።

> **አንደኛ፡** በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ የአገራችንን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ዐቅምና ፍላጐት እንደሌለውና አገራችንን ወደ ባሰ መቀመቅ ይዟት እየገባ እንደሆነ አብዛኛው የአገራችን ሕዝብ፣ ተቃዋሚው ጐራ እና ዓለም-አቀፉ ሕብረተሰብ በአሁኑ ወቅት በተሻለ ሁኔታ ተገንዝቧል።
>
> **ሁለተኛ፡** ከሁለት ዓመታት በፊት ከነበረው ሁኔታ በብዙ ርቀት በተሻለ ከገዥው ፓርቲ እና ከጥቂት “አጋር” ድርጅቶቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ኃይሎች የሽግግር መንግሥት መቋቋም አስፈላጊነትን ተቀብለዋል።
>
> **ሦስተኛ፡** በብዙ አገራትም ሆነ በአገራችን ያለፈ ታሪክ እንዳየነው ብዙውን ጊዜ የሽግግር መንግሥት የሚቋቋመው አንድ መንግሥት በሌላ አዲስ ኃይል በትጥቅ ትግል ወይም በአብዮት ተሸንፎ ከሥልጣን ሲወገድ፣ ወይም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በራሱ የውስጥ ችግር ሙሉ በሙሉ ሲፈርስ ነው። በአሁኑ የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ግን መንግሥት እንዳለ በማይቆጠርበት ሁኔታ ቢዳከምም ገና ለይቶለት አልፈረሰም። **በሆነ ‘ተዓምር’ ልቦና ቢያገኝ የብልፅግና አገዛዝ ለሽግግር መንግሥቱ መቋቋም ጥሩ እርሾ ሆኖ ሊያገለግልና የተሻለ ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል።**

እነዚህ ሦስት ሁኔታዎች ኢትዮጵያ የተሳካ የሽግግር ሒደት ማካሄድ እንድትችል የተሻለ ምቹ ሁኔታዎች የሚፈጥሩ ናቸው። አሁን ላይ **እነዚህ በጎ እርሾዎች ባሉበት ሁኔታ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ካልቻልን ግን ከዚህ የባሰ እና ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ከገባን በኋላ ይህንን ዕድል መልሰን ልናገኘው አንችልም።** አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ደካማ መንግሥት ጭራሹኑ ፈራርሶ አንድ ጊዜ መንግሥት የለሽ ሁኔታ ውስጥ ከገባን፣ ወደ ባሰ እየተላለቁ የመፈራረስ አደጋ ውስጥ የመግባት እንጂ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋምም ሆነ በሌላ አማራጭ ሀገሪቷን ከህልውና ጥፋት ለመታደግ የምንችልበት ዕድል አይኖረንም።

የወቅቱ አገዛዝ ይህንን እውነታ ተገንዝቦ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄን ቢቀበል ሒደቱን ስኬታማ በማድረግ ረገድ ቁልፍ ሚና ሊጫወት ይችላል። ምክንያቱም አሁን እየቀረበ ያለው የሽግግር መንግሥት

ጥያቄ ገዢውን ፓርቲ ሙሉ በሙሉ ከጨዋታ ውጭ የሚያደርግ ሳይሆን እሱንም ጭምር የሽግግሩ ሒደት ተሳታፊ እና የአገራችን ችግሮች የመፍትሄ አካል እንዲሆን የሚያስችል ነው።

የወቅቱ አገዛዝ ይህንን ጥያቄ ቢቀበል በዋናነት አገራችንን ከህልውና አደጋ ለመታደግ፣ ከዚያም በተጨማሪ ራሱን ከመፈራረስ ሊያድንና ወደፊት በወንጀል ተጠያቂ የመሆን ዕድሉንም በአንፃራዊነት ሊቀንስ ይችላል። **ይህንን ጥያቄ መቀበል ብልህነት እና አሸናፊነት እንጂ ከቶውንም ሽንፈት ተደርጎ ሊቆጠር አይገባውም።** ለአገራችን ብቻ ሳይሆን ለብልፅግና አገዛዝ ይህ ዓይነቱ ዕድል አንድ ጊዜ ካመለጠ ተመልሶ ሊገኝ የማይችል ወርቃማ ዕድል ነው። በንጉሱና በደርግ ዘመን ሲሆን እንደታየው አገዛዙ ይህንን ዕድል መጠቀም ተስኖት በተቃዋሚው ጐራና በሕዝቡ ትግል ተሸናፊ ከሆነ ግን የሕግ ተጠያቂ ብቻ እንጂ የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊ የመሆን እና ራሱን ከጥፋት የማዳን ዕድል አይኖረውም።

በርግጥም ጠ/ሚ ዐቢይ "አራምደዋለሁ" የሚሉት የ'መደመር' አስተሳሰብ ከአንገት ሳይሆን ከአንጀት ቢሆን ኖሮ ይህንን አማራጭ በደስታ በተቀበሉት ነበር። "እኔ አሻግራችኋለሁ!" በማለት ሌሎችን ከሒደቱ ማግለል "ከመቀነስ" ጋር እንጂ "ከመደመር" አስተሳሰብ ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም። በዚህ ሒደት አንዳችን 'አሻጋሪ'፣ ሌላችን 'ተሻጋሪ' ሳይሆን፣ ሁላችንም አሻጋሪ እና ተሻጋሪ መሆን ይኖርብናል። ዴሞክራሲ የውጤት ብቻ ሳይሆን የሒደትም ጉዳይ መሆኑ በትክክል ገብቶን ከሆነ "እኔ አሻግራችኋለሁ!" የሚለው አስተሳሰብ ፀረ-ዴሞክራሲ ነው። ይልቁንም እውነተኛ 'የመደመር' ተግባር ሊሆን የሚገባው ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄን በጸጋ በመቀበል አገርን በጋራ ተባብሮ ወደ በጐ አቅጣጫ ማሸጋገር መቻል ነው።

የሽግግር ሒደት ጥያቄን በተመለከተ "እኔ አሻግራችኋለሁ!" ከሚለው አገዛዝ ውጭም አንዳንድ ወገኖች በቅንነት የሚያቀርቡት ተቃውሞ ይኖራል። እነዚህ ወገኖች በጥያቄው ላይ የሚያቀርቡት አፀፋዊ ክርክር "መንግሥት ጥያቄውን ሊቀበለው አይችልም" ወይም "የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ከባድና ውስብስብ ስለሆነ በአገራችን ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም!" የሚል ነው። በእርግጥም ጥያቄውን መንግሥት በፀጋ እንደማይቀበለው፣ በቀላሉም መተግበር የማይችል ከባድ ጉዳይም መሆኑ ግልፅና የማያከራክር ነው። እንዲህ ዓይነቱን መከራከሪያ ማቅረብ የምንችለው ግን 'አገራችንን ከገባችበት የህልውና አደጋ ለማዳን የሚችል ሌላ አማራጭ አካል ወይም ሒደት አለ!' ብለን ካመንንና ተከራክረን ማሳመንም የምንችል ከሆነ ብቻ ነው። በአሁኑ ወቅት ሌላ አማራጭ ስለመኖሩ እንኳን ለማሳመን ለመከራከርም የሚሞክር የለም። "ብልፅግና ያሻግረናል!" ከሚለው ውሃ የማይቋጥር ክርክር በተለየ ሌላ አማራጭ መኖሩን ማሳመን እስካልቻልን ድረስ ግን መንግሥት ፈቃደኛም ሆነ አልሆነ፣ ተግባሩም ቀላል ሆነ ከባድ፣ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታችን ነው የሚሆነው።

በእኔ ዕይታ- ከሽግግር መንግሥት በታች በሆነ ሌላ አማራጭ ችግሩን ለመፍታት የነበረንን ዕድል ሁሉ ደጋግመን አሳልፈነዋል፣ አባክነነዋል። በተገቢው ጊዜ እና ሁኔታ ያልፈታናቸው ችግሮቻችን ተጠራቅመው፣ ተባብሰውና ተወሳስበው ዛሬ ላይ ከሽግግር መንግሥት በመለስ ባለ ሌላ አማራጭ የማይፈቱበትን አጣብቂኝ

በራሳችን ላይ ፈጥረናል። “የሽግግር መንግሥት አያስፈልገንም” የሚለው የአገዛዙና የደጋፊዎቹ ክርክር በተዘዋዋሪ “ስልጣናችን እንዲነካ አንፈልግም” ከማለት ባለፈ በሌላ አሳማኝ ምክኒያት ተደገፎ ሲቀርብ አላየንም።

ከገዥው ፓርቲና ከጭፍን ደጋፊዎቹ በተጨማሪ፣ በተቃዋሚው ጐራ በኩል ያሉ አንዳንድ ኃይሎች “የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ሳያስፈልግ እኛ አሸንፈን ስልጣኑን እንይዘዋለን!” የሚል ክርክር የሚያቀርቡ አሉ። ነገር ግን ተቃዋሚዎች ተጠናክረው አገዛዙን ማሸነፍ ቢችሉም እንኳ የሽግግር መንግሥት ሳያቋቁሙ በቀጥታ መደበኛ መንግሥት መመስረት የሚችሉበት ዕድል የለም። **የሕዝብ መንግሥት በሕዝብ ምርጫ እስኪቋቋም ድረስ አንዳች ዓይነት የሽግግር መንግሥት ማቋቋም የግድ ነው።** ስለሆነም በየትኛውም መንገድ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጉዳይ የማይታለፍ አጀንዳ ነው። አገዛዙ በሕዝብ ትግል ቢሸነፍም ሆነ በራሱ ውስጣዊ ቅራኔ ድንገት ቢፈራርስ የሽግግር ሒደት አስፈላጊነቱ አይቀሬ ስለሆነ ከወዲሁ “ሽግግር መንግሥት እንዴት?”፣ “በማን?” እና “ለምን?” በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የጠራ አቋም ይዞ መገኘት ወቅታዊና አስፈላጊ እርምጃ ነው።

አገራችን ወደ አዲስ የሽግግር ሒደት እንድትገባ የሚያስችል ዕድል በሦስት ኃይሎች እጅ ውስጥ አለ። ***የመጀመሪያው ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ ናቸው።*** እርሳቸው በሆነ “ተዓምራዊ” ምክንያት ‘ልቦና’ አግኝተው ከራሳቸው የሥልጣን ጥማት በላይ የሕዝብና የአገር ደህንነትን ቢያስቀድሙ ሁሉንም የፓርቲና የመንግሥት ሥልጣን በብቸኝነት ጠርንፈው የያዙ ሰው ስለሆኑ አገራችንን ወደ አዲስ የሽግግር ሒደት ለማስገባት ሰፊ ዕድል አላቸው። ባለፉት ስድስት ዓመታት በተጨባጭ ከተረዳነው የሰውየው ማንነትና ባሕርይ አኳያ ግን ይህንን ዕድል ወደ ተግባር ለመቀየር ያላቸው ፍላጐት ከዜሮ እጅ (0%) በታች ነው ማለት ይቻላል።

***ሁለተኛው ኃይል ብልፅግና ፓርቲ ነው።*** ብልፅግና ፓርቲ በራሱ ውስጠ-ደንብ የተቀመጠውን ስልጣኑን የመጠቀም የኃላፊነት ስሜትና ድፍረት ቢኖረው አገራችንን እያፈራረሷት የሚገኙትን ጠቅላይ ሚኒስተር በአንድ ቀን ጉባኤ ከሥልጣን አውርዶ አገራችንን ወደ አዲስ የሽግግር ሒደት ሊያስገባት ይችላል። እንዳለ የማይቆጠረውና የአንድ አምባገነን መሪ የመገልገያ መሳሪያ የሆነው ብልፅግና ፓርቲ ግን ይህንን መብትና ግዴታውን የመወጣት አስር እጅ (10%) የሚሆን ዕድል እንኳን ይኖረዋል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል።

***ሦስተኛውና የመጨረሻው ኃይል ተቃዋሚው ጐራ ነው።*** ተቃዋሚው ጐራ የጐንዮሽ መራኮቱን አቁሞ የሕዝብና የአገር ህልውናን ማትረፍን ቀዳሚ አጀንዳው አድርጐ ቢተባበርና ጠንካራ ህዝባዊ ትግል ማካሄድ ቢችል በሥልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ በአጭር ጊዜ አሸንፎ በምትኩ አገራችንን ወደ አዲስ የሽግግር ሒደት ሊያስገባት ይችላል። ነገር ግን ተቃዋሚው ጐራ ምን ያህል እርስ-በራሱ የማይግባባ፣ ሕዝቡን በብቃት ማታገል የሚያስችል ድርጅታዊ ብቃት ገና ያልፈጠረና የአስተሳሰብ ጥራት የሌለው ደካማ ኃይል መሆኑን ስናይ ይህንን ዓላማ የማሳካት ሃያ እጅ (20%) ዕድል እንኳን ይኖረዋል ብሎ መገመት ያስቸግራል።

‘ሁሉም በግራ-ቀኝ ያሉ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች የመፍትሄው ሳይሆን የአገራችን ጥፋት አካል ሆነዋል’ ለማለት የሚያስደፍረንም ይህ ‘ዙሪያው-ገደል’ የሆነ የአገራችን አስቸጋሪ ነባራዊ እውነታ ነው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በያዝነው የጥፋት መንገድ መጓዝ ከቀጠልን እየተላለቁ ከመፍረስ አደጋ ለመዳን የሚኖረን ዕድል ከሲሶ እጅ (⅓) የበለጠ ይሆናል ብሎ መገመት ያስቸግራል። **ዞሮ ዞሮ በሕዝብ እና በአገር ህልውና ላይ ተስፋ ቆርጦ መቀመጥ አይቻልምና ጠባቡን ዕድል አስፍቶ ለአሸናፊነት ለመብቃት እስከ መጨረሻው ጥርስን ነክሶ መታገል የግድ ነው።** የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የወቅቱ አገዛዝ በሕዝብ ትግል ተገዶ፣ ወይም በራሱ ውስጣዊ ድክመት ተፈረካክሶ ከሥልጣን መውረዱ አይቀሬ ነው።ነገር ግን ስለሚተካው አካልና ስለሚመጣው ለውጥ ከወዲሁ በቂ ዝግጅት ከሌለን የአገዛዙ መውደቅ በራሱ የመጨረሻ ውጤት አይደለም። አገዛዙ የአገርን ህልውናም አብሮ ይዞ ሊወድቅ ይችላል። ስለሆነም ይህ ክስተት ከመፈጠሩ በፊት ተቃዋሚው ጐራ በምን ዓይነት የሽግግር ሒደት አገራችንን ወደ ተሻለ አቅጣጫ ሊያስገባት እንደሚችል ከወዲሁ የጠራ አቋም ሊይዝ ይገባል።

በዚህ ላይ መግባባት ከቻልን ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለው ጥያቄ፣ በሽግግር ሒደቱ ሊቋቋም የሚችለው የሽግግር መንግሥት እንዴትና በእነማን ሊቋቋም ይችላል? ከተቋቋመ በኋላስ የሚተገብራቸው ኀላፊነቶችና የሚያሳካቸው ዓላማዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ? የሚል ይሆናል። እነዚህ ጥያቄዎች መመለስ የሚገባቸው በግለሰቦች፣ በአንድ ገዥ ፓርቲ ወይም በአንድ ሥልጣን ላይ ባለ አገዛዝ ሳይሆን በአንድ አገር በሚካሄድ ሀቀኛ እና ሁሉን-አቀፍ **አገራዊ የውይይትና የድርድር ሒደት (አውድሒ)** ብቻ ነው።

ነገር ግን የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ሲጠየቅ፣ ጥያቄው እንዲሁ በዘ-ፈቀደ እየቀረበ ያለና ጭራሹኑም በተግባር ሊፈፀም የማይችል ባዶ ቅዥት መስሎ የሚታያቸው ሰዎች በቁጥር ቀላል ስላልሆኑ እንዲህ አይነቱን ዝርዝር መነሻ ሐሳብ በዚህ መልኩ አቅርቦ ማሳየት አስፈላጊ ይሆናል። አጀንዳው የተጨበጠና መሬት ላይ ሊተገበር የሚችል መሆኑን ከማሳየትም በላይ፣ የተቃዋሚው ጐራ የአዲስ የሽግግር ሒደት አስፈላጊነትን የጋራ የመተባበሪያና የመታገያ ቀዳሚ አጀንዳው አድርጐ ሊቀበለው ይገባል።

ይህ የመነሻ ሐሳብ “የኔ አስተሳሰብ ትክክል ነውና ተቀበሉት” በሚል ግላዊ መንፈስ ከቶውንም የቀረበ አይደለም። ይልቁንም “ሁላችንንም ሊያስማማን የሚችለውና ለጋራ ህልውናችን መድህን የሚሆነው አማካይ የመፍትሄ ሐሳብ ምን ሊሆን ይገባል?” በሚል ጭንቀት ሁላችንንም የጋራ አሸናፊና ተጠቃሚ ለማድረግ ታስቦ ለውይይት የቀረበ መነሻ ሐሳብ ነው። መነሻ ሐሳብ እንደመሆኑ መጠን ለትችት፣ ለመሻሻልም ሆነ ለለውጥ ክፍት ነው። ስለሆነም መነሻ ሐሳቡን ስናነብና ለመገምገም ስንሞክር ራሳችንን ከግልና ከቡድን ጠባብ የፖለቲካ አመለካከት በማራቅ የአገርንና የሕዝብን የጋራ ጥቅም በሚያስቀድም አግባብ ልንረዳው ይገባል። ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ለመቀበል፣ ለማሳመን ብቻ ሳይሆን ለማመንም ራሳችንን ማዘጋጀት ይኖርብናል። በማንስማማባቸው ጥቂት ጉዳዮች ላይ ከማተኮር ይልቅም በሚያስማሙን በርካታ አጀንዳዎች ዙሪያ ተሰባስበን የተባበረ ትግል በማድረግ የአገዛዙን ዕድሜ ማሳጠር እና ሕዝባችንና አገራችንን ከህልውና አደጋ መታደግ ይጠበቅብናል።

# 1.የሽግግር ሒደት ምን ማለት ነው?

የሽግግር ሒደት ማለት አንድን በመደበኛ መንግሥት ለመተዳደር ያቃተው እና በፖለቲካ ቀውስ ውስጥ የወደቀን አገር ወደ ተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት ለማሸጋገር የሚካሄድ እና ከሽግግር መንግሥት የሰፋ አውድ ያለው የረዥም ጊዜ ሒደት ነው። በአገራችን መካሄድ ያለበት የሽግግር ሒደት ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚካሄድ ድርድርን፣ የሽግግር መንግሥት ከመቋቋሙ በፊት የሽግግር ቻርተር ለማውጣት የሚካሄድ ሒደትን፣ በሽግግር መንግሥቱ የስራ ዘመን የሚከናዎኑ የተለያዩ ተግባራትን እና ከሽግግሩ መንግሥት በኋላ በሕዝብ ምርጫ በሚቋቋመው መደበኛ መንግሥት የመጀመሪያ አንድ ወይም ሁለት ዓመታት ጭምር የሽግግር ሒደቱን ለማፅናት የሚሰሩ ተጨማሪ ስራዎችን የሚያካትት ሰፊ ሒደት ነው። በዚህ የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢ ግምት አጠቃላዩ የሽግግር ሒደት እስከ አምስት ዓመት የሚወስድ ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል።

# 2. የቅድመ-ሽግግር መንግሥት ሒደቶች

## 2.1. ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት

በአንድ አገር የሚካሄድ የሽግግር ሒደት ውጤታማ መሆን የሚችለው በሰከነ መንፈስ ውይይትና ድርድር ለማካሄድ የሚያስችል ሰላማዊ ምህዳር ሲኖር ነው። ስለሆነም የአገራችን የሽግግር ሒደት መጀመር ያለበት በቅድሚያ መንግሥትና በአገራችን ያሉ ሁሉም ታጣቂ የፖለቲካ ሀይሎች ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት እንዲፈርሙ በማድረግ ሊሆን ይገባል። ግጭትና ጦርነት ባልቆመበት ሁኔታ የሚካሄድ የሽግግር ሒደት ለውጤት ሊበቃ ስለማይችል የተኩስ ማቆም ስምምነት የሽግግር ሒደቱ የማይታለፍ ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል።

በተኩስ ማቆም ስምምነቱ መንግሥትና ሁሉም ፖለቲካዊ በሆነ ምክኒያት ትጥቅ አንግበው ከመንግሥት ጋር እየተፋለሙ ያሉ ታጣቂ ኃይሎች ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ የድርድሩ ተሳታፊ መሆን ይገባቸዋል። በታጣቂ ሀይሎች መካከል ከሚታየው ስር-የሰደደ አለመተማመን አኳያም ድርድሩ ሦስተኛ አካል በሆኑ የውጭ ኃይሎች አደራዳሪነት፣ እንደ አስፈላጊነቱም ከአገር ውጭ በሆነ ቦታ ሊካሄድ ይችላል። ታጣቂ ኃይሎቹ መፍትሄ የሚያሻው የፖለቲካ ጥያቄና አጀንዳ ያላቸው ስለሆኑም የተኩስ ማቆም ስምምነቱ ለአገራችን የፖለቲካ ችግር ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት በሚያስችል አግባብ መካሄድ ይገባዋል። የድርድሩ የመጨረሻ ውጤትም፡

1. ዘላቂ ተኩስ የማቆምና ሰራዊትን ወደ ጦር ካምፕ የማስገባት (ትጥቅ መፍታትን አያካትትም)፣

2. ከታጣቂዎቹ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የታሰሩ የፖለቲካና የጦር እስረኞችን የመፍታትና ምርኮኞችን የመቀያየር፣

3. በሒደት ላይ ያሉ የክስ ፋይሎችን የመዝጋት እና የሽብርተኛነት ፍረጃን የማንሳት፣

4. በቀጣይ የአገራችን ዕጣ-ፈንታ ላይ መግባባት ላይ ለመድረስ የሚያስችል የአገራዊ ውይይትና ድርድር ሒደት (አውድሒ) አስፈፃሚ ኮሚሽንን የማቋቋም፣

5. በአገራችን ፖለቲካ ተሳትፎ እያደረጉ የመቀጠል ፍላጐት ያላቸውን ታጣቂ ኃይሎች በመደበኛ የፖለቲካ ፓርቲነት የመመዝገብ፣

6. ታጣቂ ኃይሎች በካምፕ ውስጥ እንዴት መኖር እንደሚችሉና ስለ ወደፊቱ ህልውናቸው የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ እና

7. ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም አስፈላጊነት ላይ መስማማትን የሚያካትት ሊሆን ይገባል። እነዚህ ስምምነቶች በሙሉ አሁን በስራ ላይ ላለው ፓርላማ ቀርበው እንዲፀድቁ ይደረጋል።

ይህ የተኩስ ማቆም የድርድር ሒደት ከሁለት እስከ ሦስት ወር ጊዜ ሊዎስድ ይችላል።

## 2.2. የቅድመ-ሽግግር መንግሥት አገራዊ የውይይትና የድርድር ሒደት (አውድሒ)

ኢትዮጵያ ከምትገኝበት ሁለንተናዊ ቀውስ ለመውጣት አሁን ላይ አገዛዙ አካሒደዋለሁ በሚለው ዓይነት ቁንፅልና የይስሙላ የምክክር ሒደት ሳይሆን ሁሉን-አቀፍና ሀቀኛ በሆነ አገራዊ የውይይትና የድርድር ሒደት (አውድሒ) ውስጥ ማለፍ ይገባታል። የአገራችን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ ምን ይሁን? የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ በዋናነት መወሰን ያለበት በሰፊ የሕዝብና የሕዝብ ወኪሎች ተሳትፎ በሚካሄድ አገራዊ የውይይትና የድርድር ሒደት (አውድሒ) ነው። ይህንን ዓይነት የሽግግር ሒደትን የሚመለከት ሰነድ እያዘጋጀን የምናቀርብ ሰዎች ዓላማችን አጠቃላይ አቅጣጫን ለመጠቆምና የሽግግር ሒደት ማካሄድ የሚቻል መሆኑን ለማሳየት የሚያስችል የውይይት መነሻ ሐሳብ ማቅረብ ነው እንጂ የሽግግር ሒደቱ አጠቃላይ ቅርፅና ይዘት መወሰን ያለበት ሰፊ የተሳትፎ አውድ ባለው አገራዊ የውይይትና የድርድር ሒደት (አውድሒ) ነው።

በአንድ አገር የሽግግር ሒደት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ባልተቋረጠ ሁኔታ መካሄድ የሚገባው ተግባር አገራዊ የውይይትና የሽግግር ሒደት (አውድሒ) ማካሄድ ስለሆነ ሒደቱን በሦስት ምዕራፍ ከፍሎ ማካሄድ ጠቃሚ ይሆናል። የመጀመሪያው ምዕራፍ የቅድመ-ሽግግር መንግሥት አውድሒ፣ ሁለተኛው ምዕራፍ የሽግግር መንግሥት ወቅት አውድሒ፣ ሦስተኛው ምዕራፍ የድህረ-ሽግግር መንግሥት አውድሒ ይሆናል። ሌሎቹን ለጊዜው ወደ ጐን እናቆያቸውና የመጀመሪያውን ምዕራፍ እዚህ ላይ ለማየት እንሞክር።

የቅድመ-ሽግግር መንግሥት አውድሒ የሽግግር መንግሥት ከመቋቋሙ በፊት በታጠቁና ባልታጠቁ በሁሉም የአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች ተሳትፎ የሚካሄድ ሒደት ይሆናል። የዚህ ሒደት ዋና ተሳታፊዎች የተደራጁ የፖለቲካ ኃይሎች ቢሆኑም በተሳታፊዎቹ ስምምነት የተመረጡ የውጭና የአገር ውስጥ ሦስተኛ ወገኖች ሒደቱን እንዲታዘቡትና እንዲያግዙት ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል። ይህ የቅድመ-ሽግግር መንግሥት አውድሒ- በዋናነት በምን ዓይነት ተዋፅኦ የሚቋቋም፣ ምን ምን አይነት ኃላፊነቶችን የሚያከናውን፣ ምን ዓይነት ተቋማትን ያቀፈ፣ ምን ዓይነት ግቦችን የሚያሳካ እና ለምን ያህል ጊዜ የሚካሄድ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የሽግግር ጊዜ ቃል-ኪዳን (ቻርተር) ለማፅደቅ የሚካሄድ የውይይትና የድርድር ሒደት ይሆናል።

ይህንን ሒደት በዋናነት የሚያስተባብረውና የሚመራው አካልም በተኩስ ማቆሙ ስምምነት መሰረት የሚቋቋመውና በውጭ ባለሞያዎች ጭምር የሚታገዘው የአውድሒ ኮሚሽን ይሆናል። ይህ ሒደት የተኩስ ማቆም ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ በሚኖሩት ከሦስት እስከ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሊጠናቀቅ ይችላል።

# 3. የሽግግር መንግሥት

አዲስ የሽግግር ሒደት ውስጥ የመግባታችን አስፈላጊነት በዋናነት የሚመነጨው ከሁለት ምክኒያቶች ነው። የመጀመሪያውና ዋናው አገራችን ከፍተኛ የህልውና አደጋ የመግባቷ ዕውነታ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ይህ የገጠመን የህልውና አደጋ ከአንድ ገዥ ፓርቲ ዐቅም በላይ የሆነና የሁሉንም የአገራችንን የፖለቲካ ኃይሎች ስምምነትና ትብብር የግድ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። በሌላ አባባል- አገራችን የገባችበት ሁለንተናዊ ቀውስ አሁን በሥልጣን ላይ ባለው አገዛዝ ዐቅምና በመደበኛ ስርአት ወይም ከሽግግር መንግሥት ባነሰ ሌላ መንገድ መፈታት የማይችልበት ደረጃ ላይ የደረሰ በመሆኑ ነው።

የሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት አጠቃላይ ቅርፅና ይዘት መወሰን ያለበት በቅድመ-የሽግግር መንግሥቱ አውድሒ አማካኝነት በሚፀድቀው የሽግግር ጊዜ ቃል-ኪዳን (ቻርተር) መሰረት ይሆናል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለውይይት መነሻ የሚሆን ሐሳብ እንዲኖረን በሚያስችል አግባብ ምን አይነት የሽግግር መንግሥት ቢቋቋም ተገቢ ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ እንደሚከተለው ለመመለስ እንሞክር።

## 3.1. የሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት ስያሜ ምን ይሁን?

የሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት ስያሜ "የኢትዮጵያ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት"፣ ወይም በአጭሩ "የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

## 3.2. የሽግግር መንግሥቱ ኃላፊነትና ተግባር ምንድን ነው?

ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት እስካልተቋቋመ እና በፖለትካ ኃይሎች መካከል የተሻለ መግባባትና መተማመን እስካልተፈጠረ ድረስ የወቅቱ አገዛዝ በሚያስበው መንገድ አገራዊ መግባባት፣ ብሔራዊ እርቅ እና የሽግግር ጊዜ ፍትሕ ሊሰፍን አይችልም። ሕገ-መንግስት ማሻሻል፣ ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫ ማካሔድም ሆነ ሕዝብ መቁጠር አይቻልም። ስለሆነም የሚቋቋመው የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት የሚከተሉት ስድስት ዋና ዋና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

**አንደኛ፡** የአገራችንን መደበኛ የዕለት-ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ በጊዜያዊነት ማከናዎን፤

**ሁለተኛ፡** በአገራችን ሰላምና የሕግ የበላይነትን ማስፈን፤

**ሦስተኛ፡** የአገራችን የፖለቲካ ኀይሎች በመካከላቸው ባሉ መሠረታዊ የፖለቲካ ቅራኔዎች ዙሪያ ጥልቅ ውይይትና ድርድር አካሒደው በዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አገራዊ መግባባት /National Consensus/ እንዲፈጥሩ ማስቻል፤

**ዐራተኛ፡** በአገራችን ብሔራዊ እርቅ /National Reconciliation/ እንዲወርድና የሽግግር ጊዜ ፍትሕ /Transitional Justice/ እንዲሰፍን ማድረግ፤

**አምስተኛ፡** የሚፈጠረውን አገራዊ መግባባት መሰረት በማድረግ የዴሞክራሲ ተቋማትን ማቋቋምና ሕገ-መንግስታዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ፤

**ስድስተኛ፡** የሕዝብ ቆጠራ ማካሄድ

**ሰባተኛ፡** ሀገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ አካሂዳ መደበኛ የሕዝብ መንግሥት ለማቋቋም እንድትበቃ ማስቻል ይሆናል።

## 3.3. የሽግግር መንግሥቱ የሥራ ዘመን ምን ያህል ሊሆን ይገባል?

የሽግግር መንግሥቱ የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሊሆን ይችላል። ማለትም፡

**በመጀመሪያው ዓመት-** ሰላምና የሕግ የበላይነትን በመላው አገራችን ማስፈን፣ መሰረታዊ በሚባሉ አገራዊ ጉዳዮች ላይ አገራዊ መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችሉ መድረኮችን ማመቻቸት እና በሕገ-መንግሥት የማሻሻያ ጉዳዮች ላይ የውይይትና የድርድር ሒደቶችን መጀመርና ማካሄድ፤

**በሁለተኛው ዓመት-** በመጀመሪያው ዓመት የተጀመሩ ቀጣይ ስራዎችን መስራት፣ አገራዊ እርቀ-ሰላም የማውረድና የሽግግር ጊዜ ፍትሕ ማስፈን፣ የሕዝብ ቆጠራ ማካሄድ፤

**በሦስተኛው ዓመት-** በሁለተኛው ዓመት የተጀመሩ ወይም ያልተቋጩ ስራዎችን መስራት፣ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ማቋቋም፣ የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ማድረግና መደበኛ መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችል ምርጫ ማካሄድ፣ በቅደም-ተከተል ሊፈፀሙ የሚገባቸው ተግባራት ይሆናሉ።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አገራዊ የውይይትና የድርድር ሒደቱ (አውድሒ) ግን የሁሉም ተግባራት መነሻ መሰረት ስለሆነ በሽግግር ዘመኑ ሁሉም ዓመታት ሳይቋረጥ የሚካሄድ ይሆናል።

## 3.4. የሽግግር መንግሥቱ በማንና እንዴት ሊቋቋም ይገባል?

የሽግግር መንግሥቱ የሚቋቋመው በቅድመ-የሽግግር መንግሥቱ ሒደት ወቅት በአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ከሚካሔደው ውይይትና ድርድር በሚመነጨው የሽግግር መንግሥት ቃል-ኪዳን (ቻርተር) መሰረት ይሆናል። ቻርተሩ በአዋጅ መፅደቅ አለበት። አዋጁን የሚያጸድቀውም በሥራ ላይ ያለው የአገራችን ፓርላማ ይሆናል። ፓርላማው የሽግግር መንግሥቱን ቻርተር በአዋጅ ካፀደቀ በኋላም እንዲበተን ይደረጋል። በቻርተሩ መሰረት ሽግግር መንግሥቱን የማቋቋሙና የማደራጀቱ ኃላፊነትም የቅድመ-የሽግግር መንግሥቱ አውድሒ ኮሚሽን ይሆናል።

## 3.5. የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊዎች እነማን ሊሆኑ ይገባል?

በሽግግር መንግሥቱ ውስጥ የሚሳተፉት አካላት እነማን መሆን እንዳለባቸውና የተዋፅኦቸው መስፈርትና ቀመር የሚዎሰነው አስቀድሞ በሚፀድቀው የሽግግር መንግሥት ቻርተር ይሆናል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊ መሆን ያለባቸው ሦስት አካላት ቢሆኑ ተገቢ ይሆናል። እነሱም፡ በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘው ብልፅግና ፓርቲ፣ በአሁኑ ወቅት በትግል ላይ የሚገኙ ወይም በቅድመ-የሽግግር መንግሥቱ ወቅት የሚቋቋሙ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ኅብረተሰቡን በተለያየ ደረጃ ሊወክሉ የሚችሉ ማህበራት ወይም ግለሰቦች ናቸው። ግለሰቦቹ በጐ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ግለሰቦች ወይም የሕዝብ ተቋማትና ማሕበራት ተወካዮች ሊሆኑ ይችላሉ።

በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘው ገዥው ፓርቲ ለሽግግር ሒደቱ መፈጠር ፈቃደኛ በመሆን መንግስታዊ ስልጣኑን ከለቀቀ የሽግግር መንግሥቱ አንድ ተሳታፊ ይሆናል። በአገራችን የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በሙሉ የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊ ይሆናሉ። ነገር ግን በቁጥር በርካታ ስለሆኑ በሽግግር መንግሥቱ ውስጥ ሥርዓት ባለው መንገድ ተሳታፊ ለመሆን እንዲችሉ በቅድሚያ አንድ ዓይነት የጋራ

አደረጃጀት መፍጠር ይኖርባቸዋል። ማለትም ራሳቸውን ቢያንስ በሁለት ጎራ ከፍለው የራሳቸውን የጐንዮሽ ውይይትና ድርድር የሚያካሂዱበት ምክር ቤት ሊፈጥሩ ይገባል።

ለምሳሌ- የብሔር አደረጃጀትን የሚከተሉ ፓርቲዎች በአንድ ወገን፣ ህብረ-ዜግነት ወይም አገራዊ አደረጃጀትን የሚከተሉት ደግሞ በሌላ ወገን በመሰባሰብ የየራሳቸውን የጐንዮሽ ምክር-ቤቶች ሊያቋቁሙ ይችላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ራሳቸውን ወይም ሌሎች የሕብረተሰብ ተቋማትን በመወከል የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊ የሚሆኑት ማህበራትና ግለሰቦችም የራሳቸውን የጐንዮሽ ምክር-ቤት ሊያቋቁሙ ይችላሉ። ይህ መሆን ከቻለ- በአጠቃላይ የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊዎች በዐራት ጎራ ይከፈላሉ ማለት ነው። ገዥው ፓርቲ ራሱን ችሎ "ጎራ አንድ"፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፍ ሲል በተጠቀሰው የልዩነት መስፈርት መሰረት ለሁለት ተከፍለው፣ "ጎራ ሁለት" እና "ጎራ ሦስት"፣ የማህበራቱና የግለሰቦቹ ስብስብ "ጐራ ዐራት" ይሆናሉ ማለት ነው።

በሌላ አባባል በሽግግሩ መንግሥት ተሳታፊዎች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ድርድር የዐራት ጎራዎች ወይም የዐራትዮሽ ድርድር ይሆናል ማለት ነው። በተለይም ከ50 በላይ የሆኑ ፓርቲዎች ራሳቸውን ችለው በአንድ የሽግግር ሒደት በሥርዓት ሊወከሉና ሊደራደሩ የሚችሉበት ዕድል በጣም አስቸጋሪ ስለሚሆን የሽግግር መንግሥቱ እንዲቋቋም መስማማት ላይ ሲደረስ ተቃዋሚዎችም ይህንን አደረጃጀት ፈጥረው የጋራ ወኪል እየመረጡ በሒደቱ በሚፈጠሩ መዋቅሮች በአግባቡ መወከልና ሥርዓት ባለው መንገድ መደራደር ይችላሉ። ይህንን ማድረግ ቀላል ሥራ ባይሆንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከራሳቸው የፓርቲ የሥልጣን ጥያቄ በላይ የአገራችንን ህልውናና ጥቅም የሚያስቀድሙ ከሆነ በዚህ መልክ የግድ ራሳቸውን አደራጅተው መቅረብ ይኖርባቸዋል። ከዚህ ውጭ የሚኖረው አማራጭ ሁሉም ፓርቲዎች፣ ማህበራትና ግለሰቦች በተናጠል እንዲዎከሉ ማድረግ ነው። ይህ ግን ፈፅሞ አማራጭ ካልጠፋ በስተቀር የሚመረጥ መንገድ አይደለም።

ገዢው ፓርቲ ከራሱ ሥልጣን በላይ የአገራችንን ጥቅም ማስቀደም ችሎ የሽግግር መንግሥት የማቋቋሙን ጥያቄ ከተቀበለ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በበኩላቸው ከላይ የተጠቀሰውን የጐራ አደረጃጀት ተቀብለው ለመደራደር መወሰን ይጠበቅባቸዋል። እንዲያውም አብዛኛው ተቃዋሚ ኃይል ይህንን አደረጃጀት ከተቀበለ፣ ለመቀበል ፈቃደኛ የማይሆን ተቃዋሚ ፓርቲ ካለ ግን በፓርቲነት የመቀጠልና ወደፊት በሚካሔደው ሀገራዊ ምርጫ የመሳተፍ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሽግግር መንግሥቱ አካል እንዳይሆን ቢደረግ ተመራጭ ይሆናል።

ይህ ጥረት ተሳክቶ በሦስት ጎራ የተከፈሉት ፓርቲዎች በሽግግር ሒደቱ ወቅት በትብብር አብሮ የመሥራት ባሕልን መለማመድና ማዳበር ከቻሉም የመድብለ-ፓርቲ የፖለቲካ ባህል በአገራችን እንዲጠናከር የሚያስችል ሚና ይኖራቸዋል። በተጨማሪም በወደፊቱ የአገራችን የፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ የኅብረተሰቡን ጥቅምና ፍላጎት በአግባቡ መወከል የሚችሉ ሦስት ጠንካራ ሀገራዊ ፓርቲዎች ወይም ቅንጅቶች በጐላ ሁኔታ ተጠናክረው እንዲወጡ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ዕድል ሊፈጥሩ ይችላል። የአገራችን ፓርቲዎች በወደፊቱ የአገራችን የፖለቲካ ሒደት ቀላል ናቸው የሚባሉ ልዩነቶችን በውይይትና በድርድር፣ መለስተኛ

የሚባሉ ቅራኔዎችን በምርጫ ፉክክር፣ ከፍተኛ የሚባሉ ቅራኔዎችን ደግሞ በሕዝበ-ውሳኔ እየወሰኑ ለመቀጠል የሚያስችል አዲስና ዘላቂ የፖለቲካ ባህል የመለማመጃ ጅማሮ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ሒደቱም በዴሞክራሲያዊ አግባብ ሊፈታ የማይችል ቅራኔ በአገራችን በተለየ ሁኔታ እንደሌለ ሊያረጋግጥልን ይችላል።

ከገዥው ፓርቲና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች በተጨማሪ የማህበራቱና የግለሰቦቹ ስብስብም እንደ አንድ ጎራ ራሱን አደራጅቶና የራሱን መሪዎች መርጦ በሽግግሩ ወቅት በሚካሄዱ ድርድሮች የሕዝቡን የተለያዩ ጥቅሞችና ፍላጐቶች የሚያስከብሩ ድርድሮች የማድረግ ዕድል ይኖረዋል።

በተቻለ መጠን የሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት ሁሉን አካታችና አሳታፊ ሊሆን ይገባዋል። ነገር ግን ነፃ የፖለቲካ ምህዳር በአገራችን ሲፈጠር ከአግባብና ከዐቅም በላይ የሆነ የተሳትፎ ጥያቄ ሊፈጠርም ስለሚችል የተሳታፊዎች የመወከል ብቃት ሊመዘንበት የሚችል መለስተኛ መስፈርት በአውድሒ ኮሚሽኑ አማካኝነት ተዘጋጅቶ ሊተገበር ይገባል።

### 3.6. የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊዎች የውክልና ቀመር ምን ሊሆን ይገባል?

የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊዎች የውክልና ቀመር የሚዎሰነው በቅድመ-የሽግግር መንግሥቱ አውድሒ ይሆናል። በአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች መካከል በሚደረገው ድርድር በጣም አስቸጋሪ ተግባር የሚሆነውም በዚህ አጀንዳ ላይ ስምምነት ላይ መድረስ መቻል ይሆናል። ነገር ግን ሽግግር መንግሥቱን የማቋቋምና ውጤታማ የማድረግ ጉዳይ የራስንም ሆነ የአገርና የሕዝብ ህልውናን የመታደግ "የሞት-የሽረት" ጥያቄ ስለሆነ ከህልውና በታች በሆነ በማንኛውም ሌላ ጉዳይ ላይ መቻቻልን መፍጠር ግዴታ እንጂ የምርጫ ጉዳይ ሊሆን አይገባውም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንፃራዊነት ሁሉንም ተሳታፊዎች ሊያስማማ የሚችል ሚዛናዊ መስፈርት መቀመር አስፈላጊ ይሆናል። ድርድሩ ይዞት ሊመጣው ስለሚችለው ውጤት ከወዲሁ መተንበይ ባይቻልም በዚህ የውይይት የመነሻ ኃሳብ አቅራቢ አመለካከት ግን ከአራቱ የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊ ጐራዎች- ብልፅግና ፓርቲ 10%፣ ሁለቱ የተቃዋሚ ፓርቲ ጐራዎች እያንዳንዳቸው 30%፣ የማህበራቱና የግለሰቦቹ ጐራ 30% ድርሻ ቢኖራቸው ተገቢና ምክንያታዊ ይሆናል።

እዚህ ላይ ገዥው ብልፅግና ፓርቲ አንድ ፓርቲ ሆኖ እያለ እንዴት ብቻውን 10% ድርሻ ሊሰጠው ይገባል? የሚል ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። ተገቢ ጥያቄ ነው። መልሱ ግን አጭርና ግልፅ ነው። ብልፅግና ፓርቲ እስከ መጨረሻው ድረስ በያዘው የጥፋት መንገድ በመቀጠል የአገራችንን የህልውና ጥፋት አይቀሬ ከማድረግ ይልቅ የመፍትሄው አካል ለመሆን ወስኖ የሽግግር ጥያቄን በፀጋ ለመቀበል ለሚወስነው ውሳኔ ሕዝቡ እየተናነቀውም ቢሆን ለህልውናው እና ለሽግግሩ ስኬታማነት ሲል ሊከፍለው የሚገባ ዋጋ እና ውለታ ይሆናል። በአጠቃላይ በዚህ አጀንዳ ላይ ስምምነት ላይ መድረስ ከባድ ፈተና እንደሆነ ከወዲሁ መገንዘብ፣ ነገር ግን ይህ ፈተና የወደፊት ህልውናችንን የሚወስን እና የግድ መታለፍ ያለበት ፈተና መሆኑን አምኖ መቀበል ያስፈልጋል።

## 3.7. የሽግግር መንግሥቱ ምን ዓይነት አደረጃጀት ወይም መዋቅሮች ሊኖሩት ይገባል?

የሽግግር መንግሥቱ በቻርተሩ ተደንግገው የተሰጡትን ዓላማዎች ለማሳካትና ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ዝርዝር ኃላፊነቶቹን በአግባቡ ለመተግበር በፌደራል ደረጃ የሚከተሉት ሁለት መዋቅሮች ይኖሩታል።
እነሱም፡

1. የፌደራሉ የሽግግር ሸንጎ፣ እና
2. የፌደራሉ የሽግግር ስራ-አስፈፃሚ ካውንስል ናቸው።

እነዚህ ሁለት መዋቅሮች ከፍ ሲል በተቀመጠው የተሳትፎ ድርሻ ቀመር መሰረት በሽግግሩ ተሳታፊ አካላት ሚዛናዊ ተዋፅኦ የሚቋቋሙ ይሆናል።

### 3.7.1. የፌደራሉ የሽግግር ሸንጎ

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ይህ የፌደራሉ የሽግግር ሸንጎ የቅድመ-ሽግግሩ አውድሐ. የሚያወጣውን የሽግግር ጊዜ ቻርተር መሰረት አድርጐ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ባለው ፓርላማ በአዋጅ የሚቋቋም ሲሆን ለመጪዎቹ ሦስት ዓመታት ፓርላማውን ተክቶና ትልቁ የአገራችን የሥልጣን አካል ሆኖ አገራችንን በሕግ አውጭ ተቋምነት የሚመራ ሸንጐ ይሆናል። የፌደራሉ ፓርላማና የክልል ምክር ቤቶች በነጻና ፍትሃዊ የሕዝብ ምርጫ ወደፊት ተቋቁመው ከሽግግር መንግሥቱ ሥልጣን እስከሚረከቡ ድረስ የፌደራሉ የሽግግር ሸንጐ በመላው አገራችን ብቸኛ የሕግ አውጭ አካል ሆኖ ያገለግላል። ይህ ሸንጐ ከ350 እስከ 400 አባላት የሚኖሩት ሲሆን፣ አራቱ የሽግግር መንግሥቱ ተሳታፊ ጐራዎች ከላይ በተቀመጠው የተሳትፎ ድርሻ ቀመር መሰረት በሸንጐው ውስጥ ውክልና ይኖራቸዋል።

ሸንጎው ሥልጣኑን ከወቅቱ ፓርላማ ተረክቦ በሚቋቋምበት ዕለት አፈ-ጉባኤውንና ምክትል አፈ-ጉባኤውን ይመርጣል። የሚመረጡት ሁለቱ አፈ-ጉባኤዎች የፓርቲ አባል ያልሆኑ የሸንጎው አባላት ይሆናሉ። ቀጥሎም በሽግግር ዘመኑ ወቅት የአገራችን ርዕሰ-ብሔር የሚሆነውን ሰው ይመርጣል። የሚመረጠው ርዕሰ-ብሔር የሸንጐው አባል የሆነ፣ ነገር ግን የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ ሰው ሊሆን ይገባዋል። ሸንጐው ካመነበት በስራ ላይ ያሉትን ርዕሰ-ብሔር የሽግግሩ ወቅት ርዕሰ-ብሔር አድርጐ ሊያስቀጥላቸው ይችላል።

ሸንጎው በተቋቋመ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሦስት ዓመታት የሥራ ዕቅዱንና የራሱን የውስጥ አሠራር የሥነ-ሥርዓት ደንብ በዝርዝር አውጥቶ ያጸድቃል፤ ለሦስት ዓመቱ የሽግግር ጊዜ ለሽግግር መንግሥቱ በአዋጅ የተሰጡ ኀላፊነቶችን የመፈጸም ሥልጣን የሚኖረው አንድ የሽግግር ጊዜ የፌደራል የሥራ አስፈጻሚ ካውንስል ያቋቁማል።

ከሽግግር መንግሥቱና በሽግግር መንግሥቱ አማካኝነት ከሚዎጡ ህጐችና ከሚቋቋሙ ተቋማት ውጭ በአሁን ወቅት በሥራ ላይ ያሉ ሕግጋትና ተቋማት በሙሉ የሽግግር ዘመኑም ሕግጋትና ተቋማት ሆነው ይቀጥላሉ። ሸንጎው የሽግግር መንግሥቱን ኀላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና የአገራችንን ደህንነት ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም በአንዳንድ የአገራችን ተቋማት፣ ህጐችና የፖለቲካ መብቶች ላይ ጊዜያዊ እገዳ እንዲጣል የማድረግ ሥልጣን ሊኖረው ይገባል።

### 3.7.2. የፌደራሉ የሥራ-አስፈጻሚ ካውንስል

የሽግግር መንግሥቱ የሥራ አስፈጻሚ ካውንስል በሸንጎው የሚቋቋምና ተጠሪነቱም ለሸንጎው የሆነ የሽግግር መንግሥቱ የፌደራል ሥራ-አስፈጻሚ ነው። ካውንስሉ 45 አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነዚህ አባላቱ በሽግግር መንግሥቱ ዐራት ተሳታፊ ጐራዎች የውክልና ድርሻ ቀመር መሰረት ተመርጠው ሹመታቸው በሸንጐው የሚፀድቅ ይሆናሉ።

የስራ-አስፈፃሚ ካውንስሉ ከመካከሉ አንድ የሽግግር ዘመን ዋና ጠቅላይ ሚኒስትርና ሁለት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችን ይመርጣል። እነዚህ ሦስት ጠቅላይ ሚኒስትሮች ከሶስቱ የፖለቲካ ፓርቲ ጐራዎች የሚመረጡ ሲሆን ዋናው ጠቅላይ ሚኒስትር ከሦስት ዓመት በኋላ በሚካሔደው አገራዊ ምርጫ በእጩነት ቀርቦ የማይዎዳደር ሊሆን ይገባል። የካውንስሉ ሦስት ጠቅላይ ሚኒስትሮች የእርስ በርስ ድርድር አካሒደው የሽግግር መንግሥቱን ኀላፊነቶች በአግባቡ ማስፈጸም የሚችሉ ሚኒስትሮችን ይመርጣሉ፣ ስድስት ጊዜያዊ ኮሚሽኖችን ያቋቁማሉ። የሚቋቋሙት ኮሚሽኖች፡

1.የክልሎች ጉዳይ ማስተባበሪያ ኮሚሽን፣
2.የአገራዊ ደህንነት አስከባሪ እና የፀጥታ ተቋማት አደራጅ ኮሚሽን፣
3.የሽግግር ወቅት አውድሒ ኮሚሽን፣
4.የሕገ-መንግሥት ማሻሻል አስፈፃሚ ኮሚሽን፣
5.የምርጫ፣ የሕዝበ-ውሳኔና የሕዝብ ቆጠራ አስፈፃሚ ኮሚሽን፣
6.የአገራዊ እርቀ-ሰላም እና የሽግግር ጊዜ ፍትህ አስፈፃሚ ኮሚሽን ይሆናሉ።

እነዚህ ኃላፊነቶች በተቀመጡበት ቅደም-ተከተል መሰረት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ኃላፊነቶች በሁለቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ ቀሪዎቹ ዐራት ኀላፊነቶች ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ባልሆኑ ሌሎች የሥራ አስፈጻሚ ካውንስሉ አባላት (ከማህበራትና ከግለሰቦች ስብስብ) የሚመሩ ይሆናል። ካውንስሉ የሶስቱን ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ የስድስቱን ኮሚሽኖችና የኮሚሽነሮቻቸውን፣ የሚኒስትሮችን ሹመት እና የሁሉንም ተቋሟት ሥልጣንና ኃላፊነት የሚመለከቱ ደንቦችን አውጥቶ በሸንጐው ያፀድቃል። ዋናው ጠቅላይ ሚኒስተር የፌደራሉ የሽግግር ጊዜ የስራ-አስፈፃሚ ካውንስሉ መሪ ከመሆን ያለፈና የተለየ ሥልጣን እንዳይኖረው ቢደረግ ተገቢ ይሆናል።

### 3.7.4. የክልል ጉዳዮች ማስተባባሪያ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በሃያ ሰባት አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ከሁለቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች አንዱ ይሆናል። የኮሚሽኑ ሰብሳቢም ሆነ አባላት የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ድርድር ሲሆን፣ የኮሚሽኑ አባላት የሸንጎው አባላት የሆኑ ወይም ያልሆኑ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ከኮሚሽኑ ሃያ ሰባት አባላት ውስጥም ሁሉም ክልሎችና ሁለቱ የፌደራል ከተሞች አንድ አንድ ተወካዮች ይኖሯቸዋል። የዚህ ኮሚሽን ዋና ኃላፊነትም የሽግግር መንግሥቱ አስፈጻሚ አካል የሽግግሩን ሒደት በክልሎች ለማስፈጸም የሚያስችሉትን የክልል ስራ-አስፈፃሚ ካውንስሎችን ማቋቋምና የሽግግር መንግሥቱን ኀላፊነቶች አፈጻጸም መከታተል ይሆናል።

በየክልሉ (ሁለቱን የከተማ አስተዳደሮች ጨምሮ) የሚቋቋሙት ካውንስሎች ዋና ኃላፊነት የክልሎቹን የዕለት-ተዕለት ሥራ መምራት እና ከሽግግር መንግሥቱ የሚሰጡትን ተጨማሪ ኃላፊነቶች በክልል ደረጃ ማስፈጸም ይሆናል። የክልሎች የሽግግር ሥራ-አስፈጻሚ ካውንስሎች የሚያስፈጽሟቸው ዝርዝር ኃላፊነቶችና የውስጥ የአሠራር ደንቦች ተቀርጸው የሚሰጧቸው በሽግግር መንግሥቱ የክልሎች የሽግግር አስተባባሪ ኮሚሽን አማካኝነት ተረቀውና በሸንጐው ፀድቀው ይሆናል።

የክልሎች የሽግግር ሥራ-አስፈጻሚ ካውንስሎች ለሽግግር መንግሥቱ የሥራ-አስፈጻሚ ካውንስልና ለክልሎች የሽግግር አስተባባሪ ኮሚሽኑ ጣምራ ተጠሪነት ይኖራቸዋል። በሽግግር መንግሥቱ የተለያዩ መዋቅሮች ውስጥ ክልሎችንና የከተማ መስተዳድሮችን የሚወክሉ አባላትን የመምረጥና የመወከል መብት የሚኖረውም ይህ የክልል የሽግግር ሥራ-አስፈጻሚ ካውንስል ይሆናል። በዚህም ምክንያት ከሁሉም ኮሚሽኖች ቀድሞ መቋቋም የሚገባው ይህ ኮሚሽን ሊሆን ይገባል። ነገር ግን የሕዝብ ቋሚ መንግሥት በምርጫ እስከሚቋቋም ድረስ ለፌደራሉም ሆነ ለክልል ጉዳዮች ሕግ የማውጣት ብቸኛ መብት የሚኖረው የሽግግሩ የፌደራል ሸንጐ ብቻ ይሆናል። የሽግግሩ መንግስት ጊዜያዊ እንጅ መደበኛ መንግሥት ስላልሆነ፣ ኃላፊነቶቹንም በልዩ ሁኔታ፣ ጥንቃቄ እና ፍጥነት መፈፀም ስለሚጠበቅበት መደበኛ መንግሥት እስከሚቋቋም ድረስ የሚከተለው አደረጃጀትና አሰራር ወደ ማዕከላዊነት ያደላ ቢሆን ይመረጣል።

### 3.7.5. የአገራዊ ደህንነት አስከባሪ እና የፀጥታ ተቋማት አደራጅ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በሃያ ሰባት አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ከሁለቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች አንዱ ይሆናል። የኮሚሽኑ አባላት የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ድርድር ሲሆን የሚመረጡት አባላት የሸንጎው አባላት የሆኑ ወይም ያልሆኑ ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኞቹ ለዚህ ኮሚሽን የሚመረጡ ሰዎች በጸጥታና በውጭ ጉዳይ ሥራ በቂ ልምድና ዕውቀት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል። የአገሪቱ መከላከያ ኤታማዦር ሹም፣ የደኅንነት ቢሮ ኀላፊ፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የዚህ ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ። አስራ አንዱ ክልሎችና ሁለቱ የፌደራል ከተሞች በዚህ ኮሚሽን ውስጥ አንድ አንድ

ተወካይ ይኖራቸዋል። ነገር ግንከሽግግሩ ሽንነ ጀምሮ በተዋረድ ባሉ መዋቅሮች ውስጥ የክልሎች በቂ ተሳትፎ መኖር ታሳቢ መደረግ አለበት።

የዚህ ኮሚሽን ዋና ኀላፊነት የሽግግር መንግሥቱ በተቋቋመ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ እስከ ቀበሌ አስተዳደር ድረስ ባለው የአገራችን መዋቅር የራሱን "የሰላምና የሕግ የበላይነት አስከባሪ ኮሚቴዎች" አቋቁሞ በመላ አገራችን ሰላምንና የሕግ የበላይነትን ፈጣንና አስተማማኝ በሆነ መጠን ማረጋገጥ ይሆናል። በሽግግሩ ወቅት ማንኛውም በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ያለ የጸጥታ ተቋም (ሚሊሻን ጨምሮ) በወጥነት የሚታዘዘው በዚህ ኮሚሽንና ይህ ኮሚሽን በተዋረድ በሚያቋቁማቸው የእዝ ኮማንዶች ብቻ ይሆናል። ኮሚሽኑ የአገር ውስጥን ጸጥታ ከማስከበር በተጨማሪ አገራችንን ከማንኛውም ዓይነት የውጭ ኃይሎች ጣልቃ-ገብነትና ጥቃት የመጠበቅ ኀላፊነት ይኖረዋል። በቂ መተማመን ከተፈጠረ በኋላ ታጣቂ ኃይሎች ትጥቅ እንዲፈቱ፣ ወይም የአገራችን የፀጥታ ተቋማት አካል እንዲሆኑ፣ ወይም ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀሉና እንዲቋቋሙ የማድረጉ ኃላፊነትም የዚህ ኮሚሽን፣ ወይም ኮሚሽኑ በስሩ የሚያቋቁማቸው መምሪያዎች ሊሆን ይገባል።

### 3.7.6. የሽግግር ወቅት አውድሒ ኮሚሽን

የሽግግሩ ወቅት አውድሒ ኮሚሽን ሃያ ሰባት አባላት የሚኖሩት ሲሆን፣ እነዚህ አባላቱም ሙሉ በሙሉ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ያልሆኑ ይሆናሉ። ከኮሚሽኑ ሰብሳቢ በስተቀርም ማንኛውም የሸንጐው ወይም የስራ-አስፈፃሚ ካውንስሉ አባላት የዚህ ኮሚሽን አባል አይሆኑም።

በሽግግሩ ሒደት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ባልተቋረጠ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆነው የአገራዊ የውይይትና የድርድር ሒደት (አውድሒ) ነው። ማለትም የቅድመ-ሽግግር መንግሥት፣ የሽግግር ወቅት እና የድህረ-ሽግግር መንግሥት አውድሒ ይኖራል።

ቅድመ-የሽግግር መንግሥት አውድሒ የአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች የሽግግር መንግሥት ከመቋቋሙ በፊት የሽግግር መንግሥቱን የቃል-ኪዳን ሰነድ (ቻርተር) ለማውጣት የሚያደርጉትን ውይይትና ድርድር የሚመራና የሚያስተባብር ይሆናል።

የሽግግሩ ወቅት አውድሒ ደግሞ በሦስት ዓመቱ የሽግግር ዘመን ስምምነት ላይ ሊደረስባቸውና ውሳኔ ሊሰጥባቸው በሚገቡ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሕዝብና የሕዝብ ወኪሎች የሚወያዩበት፣ የፖለቲካ ኃይሎች ተወያይተውና ተደራድረው ለስምምነት የሚበቁባቸውን መድረኮች መፍጠር ነው። የሽግግር ሒደቱ አውድሒ አገራዊ በሆኑ ቁልፍ ጉዳዮች ዙሪያ የሚካሄዱትን አብዛኛዎቹን የውይይትና የድርድር ሒደቶች ማስተባበርና ማስፈፀም የሚጠበቅበት ተቋም ስለሆነ ከሁሉም ኮሚሽኖች ጋር በትብብር እና በጣምራነት ይሰራል።

የድህረ-ሽግግር መንግሥቱ አውድሒ በሕዝብ የተመረጠ መደበኛ መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ በሚኖሩት አንድ ወይም ሁለት ዓመታት የሚተገበር ሲሆን ዋና ዓላማውም በሽግግር መንግሥቱ የስራ ዘመን ያልተጠናቀቁ ቀሪ ተግባራትን በማከናወን አጠቃላይ የሽግግሩን ሒደት የማፅናት ስራ መስራት ይሆናል። በሌላ አባባል- በሕዝብ ምርጫ የሽግግሩን መንግሥት ተክቶ ሥልጣን የሚይዘው የመጀመሪያው መደበኛ መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን የመጀመሪያው አንድ ወይም ሁለት የስራ ዘመኑ ዓመታት እንደ የሽግግሩ ሒደት ቀጣይ ጊዜ ይቆጠራሉ ማለት ነው።

የሽግግር መንግሥቱ በቅድመ-የሽግግር መንግሥቱ ወቅት የተቋቋመው የአውድሒ ኮሚሽን ባለበት እንዲቀጥል ወይም በአዲስ መልክ እንዲቋቋም ሊያደርግ ይችላል።

### 3.7.7. የሕገ-መንግሥት ማሻሻል አስፈፃሚ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በሃያ ሰባት አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢ የፓርቲ አባል ያልሆነና በሕገ-መንግሥት ጉዳዮች ላይ በቂ ዕውቀት ያለው ሰው ይሆናል። የኮሚሽኑ አባላት የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮችና በግለሰቦች ስብስብ ጎራው ሰብሳቢ ድርድር ሲሆን የሚመረጡት አባላት የሸንጎው አባላት የሆኑ ወይም ያልሆኑ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

አብዛኞቹ የዚህ ኮሚሽን አባላት የሕግና የፖለቲካ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ። በዚህ ኮሚሽን ውስጥ ዐራቱ ተደራዳሪ ጎራዎች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ተወካይ ይኖራቸዋል። ከኮሚሽኑ ሃያ ሰባት አባላት ውስጥም አስራ አንዱ ክልሎችና ሁለቱ የፌደራል ከተሞች አንድ አንድ ተወካዮች ይኖሯቸዋል። የዚህ ኮሚሽን ዋና ኃላፊነት ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከክልሎች ጋር በመወያየት፣ የተለያዩ የሕዝብ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የሕግ ዕውቀት ያላቸውን ምሁራንን በማወያየት፣ የሌሎች አገራትን ልምድ በመቅሰም አንድ የሕገ-መንግሥት የማሻሻያ ረቂቅ ሐሳብ አዘጋጅቶ ለሽግግሩ ሸንጎ ማቅረብ ይሆናል። ኮሚሽኑ በሚያካሒደው ጥናትም ማሻሻያ ሊደረግባቸው የሚገቡ ሕገ-መንግሥታዊ አንቀጾችን በሚከተሉት ሁለት ደረጃዎች ከፍሎ ለሸንጎው ያቀርባል። ማለትም፡

- **ደረጃ 1 ማሻሻያ፡** አነስተኛና መለስተኛ ክብደት አላቸው ተብለው የሚታመንባቸው የሕገ-መንግሥት የማሻሻያ አንቀጾች (ሶስቱ የፖለቲካ ፓርቲ ጐራዎች በድርድር የሚስማሙባቸው) ለሽግግሩ ሸንጐ ቀርበው ከሦስት ዐራተኛ ባላነሰ ድምፅ እንዲሻሻሉ ያደርጋል።

- **ደረጃ 2 ማሻሻያ፡** በደረጃ 1 ማሻሻያ አግባብ ሊሻሻሉ የማይችሉና ሶስቱ የፖለቲካ ጎራዎች መስማማት ያልቻሉባቸው የሕገ-መንግሥት አንቀጾች በሕዝበ-ውሳኔ እንዲሻሻሉ የሚያስችል የውሳኔ-ሐሳብ ለሸንጎው ያቀርባል።

የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽኑ በአጠቃላይ ሊሻሻሉ የሚገባቸውን አንቀጾች ከፍ ሲል በተጠቀሱት ሁለቱ ደረጃዎች ተለይተው ለሸንጎው እንዲቀርቡ የሚያደርገው ዐራቱን ተደራዳሪ ጎራዎች አደራድሮ ከሚያገኘው ውጤት በመነሳት ይሆናል። ነገር ግን ከአራቱ ተደራዳሪ ጐራዎች ውስጥ ሶስቱ የፖለቲካ ፓርቲ ጐራዎች በጋራ የተስማሙባቸው ጉዳዮች ተቀባይነት ይኖራቸዋል። ኮሚሽኑ በሚያቀርባቸው ረቂቅ ሐሳቦች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የሚኖረው የሽግግር ሸንጎው ሲሆን፣ ሸንጎው ከላይ በተጠቀሱት በሁለት ደረጃዎች እንዲሻሻሉ የወሰናቸውን ሕገ-መንግሥታዊ አንቀጾች ህዝባዊ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለምርጫ፣ ሕዝበ-ውሳኔ እና ህዝብ ቆጠራ አስፈፃሚ ኮሚሽኑ ያስረክባል። በደረጃ 2 የሕገ መንግሥቱ ማሻሻያ መፅደቅ የሚገባባቸው የሕገ መንግሥት አንቀፆች እንዲፀድቁ የሚደረገው በሕዝብ በተመረጡ የሕዝብ ተወካዮች ሸንጐ አማካኝነት ሳይሆን በቀጥታ በምላተ ሕዝቡ በሚካሄድ ሕዝበ-ውሳኔ ቢሆን ይመረጣል። የፓርቲ ካድሬዎች በሕዝብ ውክልና ስም የፓርቲ ፕሮግራምን የአገር ሕገ መንግሥት ሲያደርጉ ያየንበት የ1987 ዓመተ ምህረቱ ሁኔታ በአገራችን መደገም የለበትም። እንዲህ ዓይነቱን የሕዝበ-ውሳኔ አሰራር መከተልም ከፍተኛ ሕገመንግስታዊ ጉዳዮች በፖለቲከኞች አብላጫ ድምፅ እንዳይወሰኑ ስለሚያደርግ ፓርቲዎች በውክልና ቀመሩ በቀላሉ እንዲስማሙ ሊያበረታታ ይችላል።

### 3.7.8. የምርጫ፣ የሕዝበ-ውሳኔና የሕዝብ ቆጠራ አስፈጻሚ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በአስራ አንድ አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢም ሆነ አባላት የፓርቲ አባላት ያልሆኑና በገለልተኝነታቸውና ባላቸው ጥሩ ስነ-ምግባር የሚታወቁ ሰዎች ይሆናሉ። እነዚህ የኮሚሽኑ አባላት የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮችና በማህበራቱ እና በግለሰቦች ጎራው ሰብሳቢ የዐራትዮሽ ድርድር ሲሆን፣ የኮሚሽኑ አባላት የሸንጎ አባላት የሆኑም ሆነ ያልሆኑ ሰዎች ሊሆኑ ይችላል። የዚህ ኮሚሽን ኀላፊነቶች በዋናነት ዐራት ናቸው። እነሱም፡

**አንደኛ፡** የሕዝብ ቆጠራ ማካሄድ፣

**ሁለተኛ፡** የፖለቲካ ፓርቲዎች በድርድር ሊስማሙባቸው ባልቻሉ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ጉዳዮች ላይ ሕዝበ-ውሳኔ ማስጠት፣

**ሦስተኛ፡** በአጐራባች ክልሎች መካከል ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች የመፍትሄ ሐሳብ ማመንጨትና በሸንጐው አፀድቆ መተግበር፤

**ዐራተኛ፡** በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ አካሂዶ የሕዝብ መንግሥት ማቋቋም ናቸው።

በአጠቃላይ የሽግግር መንግሥቱ የስራ ዘመን የሚጠናቀቀው ይህ የምርጫ ኮሚሽን በሕዝብ የተመረጠው ቋሚ መንግሥት ሥልጣኑን ከሽግግር መንግሥቱ እንዲረከብ በሚያደርጉበት ዕለት ይሆናል። ነገር ግን

በሕዝብ የሚመረጠው መንግሥት ካመነበት የሽግግሩ የምርጫ፣ የሕዝበ-ውሳኔ እና የሕዝብ ቆጠራ አስፈጻሚ ኮሚሽን ቋሚ ተቋም ሆኖ እንዲቀጥል ሊያደርግ ይችላል።

### 3.7.9. የእርቀ-ሰላምና የሽግግር ጊዜ ፍትህ አስፈጻሚ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በ45 አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢም ሆነ አባላቱ የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ምክክርና ድርድር ይሆናል። የዚህ ኮሚሽን ሰብሳቢም ሆነ አባላት ሙሉ በሙሉ የፓርቲ አባል ያልሆኑ ሰዎች ይሆናሉ። በዚህ ኮሚሽን ውስጥ የሸንጎ አባል የሆኑም ሆነ ያልሆኑ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች፣ "የዳያስፖራ" ተወካዮች፣ የሕግ ምሁራንና በጐ ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ ታዋቂ ስፖርተኞችና አርቲስቶች፣ እና ሌሎችም... በቂ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሊደረግ ይገባል።

የዚህ ኮሚሽን ዋና ዋና ኀላፊነቶችም

- ባለፉት ሰላሳ ሦስት ዓመታት ከሰብዓዊ መብት ጥሰት ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ ወንጀሎች በምን አግባብ መፈታት እንዳለባቸው የተለያዩ የፍትህ፣ የይቅርትና የምህረት አሰጣጥ አማራጮችን የሚያመላክት ረቂቅ-ሐሳብ አዘጋጅቶ ለሸንጎው ማቅረብ፣

- በፍርድ ቤት እንዲታዩ የተወሰኑ የወንጀል ጉዳዮችን የሚያይ ልዩ የፍትህ ተቋም ማቋቋምና የሒደቱን አፈፃፀም መከታተል፣

- በሥልጣን ላይ የነበሩ ሰዎች ስለፈጸሚቸው ወንጀሎችና በደሎች መጸጸታቸውን በፈቃዳቸው የሚገልጹባቸውና ተበዳዮችም ስለደረሰባቸው በደል በይፋ ምስክርነታቸውን የሚገልጹባቸው መድረኮች በተለያዩ የአገራችን ከተሞች ማዘጋጀት፣

- በሥራ ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከአሁን በኋላ የሚያካሂዱት የፖለቲካ ትግል ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ብቻ እንደሚሆን ለሕዝቡ ቃል-ኪዳን የሚገቡባቸውን መድረኮች ማዘጋጀት፣

- እስካሁን በግጭት ውስጥ ላለፉ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የኅብረተሰብ ክፍሎች የውይይትና የይቅርታ መጠያየቂያ መድረኮችን ማዘጋጀት እና

- እነዚህን ተግባራት ሕዝቡን በሰፊው በሚያሳትፍ አግባብ በማከናወን በአገራችን አዲስ የሰላም፣ የፍቅርና የመተባበር ድባብ እንዲፈጠር ማስቻል ናቸው።

በመጨረሻም ይህ ኮሚሽን የሽግግር መንግሥቱን ታሪካዊ ስኬት በሚመለከት በብሔራዊ በዓልነት ሊከበር ስለሚገባው ቀንና በመታሰቢያነት ሊቆም ስለሚገባው የእርቅና የአንድነት ሀገራዊ ኃውልት መነሻ-ሐሳብ ለሽግግሩ ሸንጐ አቅርቦ ያፀድቃል። የሽግግር መንግሥቱ ኃላፊነቱን አጠናቅቆ በሕዝብ ለተመረጠው መንግሥት ሥልጣኑን በሚያስረክብበት ዕለት በሸንጎው ውሳኔ በተመረጠው ቦታ ላይ የኃውልቱ የመሠረት ድንጋይ እንዲቀመጥ ያደርጋል። መጭው ትውልድ ይማርባቸው ዘንድም የኮሚሽኑን አጠቃላይ የሥራ ሒደትና በአጠቃላይም የሽግግር ሒደቱን አፈጻጸም የሚያሳዩ መረጃዎች በአግባቡ ተቀርጸውና ተሰድረው በልዩ ቤተ-መዘክር ለእይታ እንዲቀመጡ ያደርጋል።

**ወገኖቼ- ከእንግዲህ ህዝባችን ከባሰ እልቂት፣ አገራችን ከመፈራረስ፣ እኛ የአገራችን የፖለቲካ ልሂቃኑም ከታሪክና ከትውልድ ተጠያቂነት ልንድን የምንችለው እንዲህ አይነቱን የሽግግር ሒደት በተባበረና ጽናት ባለው ትግል ተፈፃሚ በማድረግ ብቻ ነው።**

ልደቱ አያሌው

ሚያዚያ 30 ቀን፣ 2016 ዓ.ም.

# ከሰነዱ ውስጥ የተወሰዱና አወዛጋቢ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የተገመቱ ነጥቦች

1. ከእንግዲህ የወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ቀውስ በዘላቂነት ሊፈታ እና እየተላለቁ ከመፍረስ የህልውና አደጋ ልንተርፍ የምንችለው ሁሉን-አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግሥት በማቋቋም ብቻ ይሆናል።
2. ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት ካልተቋቋመ በስተቀር “አገራዊ ምክክር” በሚባል ቁንፅል ሒደት እውነተኛ አገራዊ መግባባት መፍጠር፣ ብሄራዊ እርቅ ማውረድ፣ የሽግግር ጊዜ ፍትህ ማስፈን፤ ሕገ-መንግሥት ማሻሻል፣ ፍትሃው ምርጫ ማካሄድም ሆነ የሕዝብ ቆጠራ ማካሄድ አንችልም።
3. ከህልውና ጥፋት ለመዳን የሚያስችለን ከፊታችን ያለ ብቸኛ አማራጭ ሁሉን-አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ቢሆንም፣ ነገር ግን ገዥም ፓርቲም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ትክክለኛው የመፍትሄ አቅጣጫ ላይ ስላልሆን ወደ ትክክለኛ የሽግግር ሒደት ለመግባት ያለን እድል ከሲሶ እጅ (30%) በላይ የሚሆን አይመስልም።
4. የወቅቱ አገዛዝ በራሱ ፈቃድ ስልጣን ቢለቅ፣ ወይም በራሱ ውስጣዊ ችግር ቢፈራርስም ሆነ በሕዝብ ትግል ቢሸነፍ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም አስፈላጊነት ሊታለፍ የማይችል አይቀሬ ሒደት ስለሆነ “ምን ዓይነት ሽግግር ያስፈልገናል?” በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ተቃዋሚው ጐራ ከወዲሁ የጠራ አቋም ሊይዝ ይገባል።
5. ወደ አዲስ የሽግግር ሒደት ከመገባቱ በፊት በአገሪቱ ያሉ ሁሉም ታጣቂ የፖለቲካ ኃይሎች ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት ላይ (ትጥቅ መፍታትን ሳይጨምር) መድረሳቸው የማይታለፍ ቅድመ-ሁኔታ መሆን ይገባዋል።
6. ብልፅግና ፓርቲ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም እየቀረበ ያለውን ጥያቄ የበለጠ የደም መፋሰስ ከመከሰቱ በፊት ከተቀበለ የሽግግር መንግሥቱ አንድ አካል ሊሆን ይገባል።
7. በሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት ውስጥ ብልፅግና ፓርቲ 10%፣ ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በድምሩ (ከ50 በላይ የሚሆኑ) 60%፣ ሌሎች ሕዝባዊ ማሕበራትና በጐ ተፅእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች 30% የውክልና ድርሻ ቢኖራቸው ተገቢ ይሆናል።
8. የሽግግር መንግሥቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚሆነው ሰው የስራ-አስፈፃሚ ካውንስሉ ዋና ሰብሳቢ ከመሆን ያለፈና የተለየ ስልጣን የሌለው እና ወደፊት በአገሪቱ በሚካሄድ መደበኛ ምርጫ የማይወዳደር ቢሆን ተገቢ ይሆናል።
9. የፖለቲካ ኃይሎች በድርድር ሊስማሙባቸው የማይችሉ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ አንቀፆች መሻሻል የሚገባቸው የሕዝብ ተወካዮች በሆነ ጉባኤ (እንደ 1987ቱ) ሳይሆን ቀጥተኛ በሆነ ሕዝበ-ውሳኔ /Referendum/ ሊሆን ይገባል።

10. የሽግግር መንግሥቱ ሸንጐ በአገሪቱ ብቸኛ ሕግ አውጭ አካል ሆኖ ሊሰራ ይገባል።
11. የሽግግር መንግሥቱ ሸንጐ ሽግግሩን ስኬታማ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በአንዳንድ የአገሪቱ ተቋማትና የፖለቲካ መብቶች ላይ እገዳ የመጣል ስልጣን እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።
12. የሽግግር መንግሥቱ ከሚያቋቁማቸው ጊዜያዊ ተቋማት እና ከሚያወጣቸው ጊዜያዊ ሕግጋቶች በስተቀር በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ያሉ ተቋማትና ህጐች የሽግግር ዘመኑ ተቋማትና ህጐች ሆነው ሊቀጥሉ ይገባል።
13. በሽግግር ዘመኑ ወቅት ሁሉም እስከ ቀበሌ ድረስ በአገሪቱ ያሉ የፀጥታ አስከባሪ ተቋማት (ሚሊሻን ጨምሮ) የሚመሩትና የሚታዘዙት በሽግግር መንግስቱ የአገር ደህንነትና ሰላም አስከባሪ ኮሚሽንና በተዋረድ በሚያቋቁማቸው የሰላምና የሕግ አስከባሪ ኮሚቴዎች ብቻ ሊሆን ይገባል።
14. መደበኛ መንግስት እስኪቋቋም ድረስ የሽግግር ዘመኑ መዋቅሮች አሰራር በአመዛኙ  የተማከለ ቢሆን የተሻለ ይሆናል።
15. በሽግግር መንግስቱ ከሚቋቋሙት ተቋማት መካከል የአገራዊ የውይይት እና የድርድር ሒደት(አውድሂ)፣ የብሄራዊ እርቅ እና የሽግግር ጊዜ ፍትህ ፣ የምርጫ፣ የሕዝበ-ውሳኔ እና የሕዝብ ቆጠራ አስፈፃሚ ኮሚሽኖች ውስጥ የፖለቲካ ተሳትፎ ያላቸው ሰዎች አባል እንዳይሆኑ ሊደረግ ይገባል።
16. በአገሪቱ የሚካሄደው አጠቃላይ የሽግግር ሒደት አምስት ዓመት፣  የሽግግር መንግስቱ የስራ ዘመን ደግሞ ሦስት ዓመት ቢሆን ተገቢ ይሆናል።
17. የሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግስት መቋቋም አጀንዳን ሁሉም በአገሪቱ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች የጋራ የመሰባሰቢያና የመታገያ ዋና አጀንዳቸው ሊያደርጉት ይገባል።

## በዚህ የውይይት መነሻ-ሐሳብ በመገናኛ ብዙሃን የሚካሄዱ ግምገማዎች እና ትችቶች ላይ ሊነሱ የሚጋባቸውን ጥያቄዎች እና አቀራረባቸውን በተመለከተ የቀረበ ጠቋሚ ሐሳብ

1- በመጀመሪያ- ከገባንበት የፖለቲካ ቀውስ ለመውጣት ሽግግር መንግስት ማቋቋም መፍትሄ ነው ብለው ያምናሉ?

2- መፍትሄ አይደለም ከተባለ ለምን? ከቀውሱ ለመውጣት የሚያስችለን ሌላ አማራጭ መፍትሄ አለ? አለ ከተባለ መፍትሄው በተጨባጭ ምንድን ነው?

3- የሽግግር መንግሥት ማቋቋም መፍትሄ ነው ከተባለ- የማቋቋሙን እድል ሊፈጥር የሚችለው ማነው? ጠ/ሚ ዐቢይ፣ ብልፅግና ፓርቲ፣ ወይስ ተቃዋሚው ጐራ? በዚህ ረገድ መነሻ ሐሳቡ ላይ በቀረቡት የመቶኛ ግምቶች ይስማማሉ?

4- ታጣቂ ኃይሎች በሚደርሱበት የዘላቂ የተኩስ ማቆም ድርድር ወቅት ስምምነት ላይ ሊደረስባቸው ይገባል ተብለው በተዘረዘሩት ሰባት ነጥቦች ይስማማሉ? መጨመር ወይም መቀነስ ያለበት ስምምነት አለ?

5- በቅድመ-የሽግግር መንግስቱ አገራዊ የውይይትና የድርድር ሂደት (አውድሂ) ወቅት የሽግግር ጊዜ ቃል-ኪዳን(ቻርተር) መዘጋጀት አለበት በሚለው ሐሳብ ምን ያህል ይስማማሉ?

6- የሽግግር መንግስቱ ተሳታፊዎች እነማን መሆን አለባቸው? ጠ/ሚ ዐቢይ ወይም/እና ብልፅግና ፓርቲ የሽግግር መንግስቱ ተሳታፊ መሆን አለባቸው? በመነሻ ሰነዱ ላይ የቀረበውን የተሳታፊዎች ማንነትና የውክልና ቀመርስ ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ?

7- የሽግግር መንግሥቱ ተግባራት ተብለው በተዘረዘሩት 6 ሀላፊነቶች ይስማማሉ? መጨመር ወይም መቀነስ ያለበት ተግባርስ አለ ብለው ያስባሉ?

8- የሽግግሩን ተግባራት ለማስፈፀም መቋቋም አለባቸው ተብለው በተዘረዘሩት 8 ተቋማት አስፈላጊነት ይስማማሉ? መጨመር ወይም መቀነስ ያለበት ተቋም ወይም ኮሚሽን አለ ብለው ያስባሉ?

10- የሽግግር መንግስቱ የስራ ዘመን ሶስት ዓመት በመሆኑ ይስማማሉ?

11- በመነሻ ሐሳቡ ሰነድ ላይ የአለዎት አጠቃላይ ግምገማ (ጠንካራና ደካማ ጐን ላይ) ምንድን ነው?

12- የሽግግር መንግሥት አስፈላጊነት የተቃዋሚው ጐራ የጋራ ጥያቄና የመታገያ አጀንዳ መሆን ይገባዋል ብለው ያምናሉ?

### ማሳሰቢያ-

**-በገምጋሚነት እና በተችነት የሚቀርቡት ሰዎች ቁጥር 2 እና ከ2 በላይ ቢሆኑ፣ በአገሪቱ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይም የተለያየ ምልከታ ያላቸው ሰዎች ቢሆኑ ተመራጭ ይሆናል።**

**- እነዚህ አቀራረቦች እንደ አንድ የአቀራረብ አማራጭ የቀረቡ እንጅ አወያዮቹ በመረጡትና በአመቻቸው መንገድ ውይይቱን የማካሄድ ሙሉ ነፃነት አላቸው።**